# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

20

- ★ ከተተፋ አይቀርር
- ★ አርሶ አደሩ ፤ ትናንትና ዛሬ
- ★ ሴቶችና ቢሮክራሲ
- ★ ደም በደም ይነፃል

የካቲት ፲፰—፲፱፻፷፱ ዓ. ም.

## ር እ ስ አ ን ቀ ጽ

# « ከ·ተተፋ አይቀር . . . »

« ኢ.ህ.አፓ የተባለው የተማሪዎችና የሀብታም ከበርቴዎች የግራ ምሥጢራዊ ቡድን ነው » ይላል ታይም የተባለው የታወቀው የኢምፔሪያሊስቶች ጋዜጣ ባለፈው ሳምንት ባወጣው እትሙ። ኢምፔሪያሊስቶች ታክቲክ መለወጥ ያሉት ነው ። ይህ አባባል በትክክለኛ ፀረ—አብዮት ትርጉሙ እንደገባን ባለፉት ወራት ስለጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥትና ስለ ኢ.ህ.አ.ፓ. የኢምፔሪያሊስት ጋዜጦች ይነዙ የነበረው ፕሮፓጋንዳ ምን እንደሆነ መመልከት ያስፈልጋል ።

አድኃሪ ኃይሎች የኢትዮጵያ አብዮት ቤት ንብረታቸውን ፣ መሬታቸውን ፣ ሥልጣናቸውን ገፎባቸዋልና የዚህን አብዮት ምንነትና ሐቀኛነት በደንብ አድርገው ይረዱታል ። ነገር ግን የአፍሪካ ተራማጆችና ጭቁን ሕዝቦች የሶሻሊስት አገሮችና የዓለም ተራማጅ ሕዝቦች የአብዮታችንን ትክክለኛ ገጽታ እንዳይረዱ ከፍተኛ የማጥላላት ዘመቻ ያካሂዱ ነበር ። በዚህ ፕሮፓጋንዳ መሠረት ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥትን «ፋሽስት» ብሎ በመጥራት ኢ.ህ.አ.ፓ. የተባለው ድርጅት ደግሞ «የኮሙኒስቶች ኮሚኒስት» «አብዮታዊ» «ማርክሲስት ሌኒንስት» እያሉ በጭቁን ሕዝቦች ፊት ይከቡት ነበር ።

ይህ የኢምፔሪያሊስቶች ፕሮፓጋንዳ ለተወሰነ ጊዜ የኢትዮጵያ አብዮት በዓለም አቀፍ ደረጃ ብቸኛ አድርጎት እንደነበረ የማይታበል ሐቅ ነው ። በዚህ በፊውዳሊዝም ጨለማ በታሠረች አገር ከታወቁ የሩሲያ አብዮት ወዲህ በታሪክ ተወዳዳሪነት የሌለው ሥር ነቀል የመሬት አዋጅ አውጆ ፣ ለብዙ ሺህ ዘመናት አንሰራፍቶ የቆየውን የዘውድ አገዛዝ ገርስሶ የከተሞች ቦታና ትርፍ ቤቶችን ወደ መንግሥት እጅ አዙሮና ለወዝአደሩ እስከ ሃምሳ በመቶ ድረስ የቤት ኪራይ ቀንሶ ፣ ታላላቅ የማምረቻና የማከፋፈያ ድርጅቶችን ከኢምፔሪያሊስቶች ወርሶ ፣ በዚች በፊውዳል ርእዮተ ዓለም በተውተበተበች አገር ማርክሲዝም ሌኒንዝምን የአብዮቱ የይፋ መመሪያ አድርጎ ፣ የአካባቢውን ፀረ—አብዮት ኃይሎች በሙሉ አርበድብዶ ፣ እነዚህን ሁሉ ድሎች ለማረጋገጥ እጅግ የተፋፋመ የመደቦች ትግል መካሄዱን በመካድ በኢትዮጵያ የሰፈነው ሥርዓት በጠቅላላው ሕዝብና በተለይ በአብዮታውያን ላይ የወረደ ፋሽስታዊ አመጽ በማስመሰል ኢምፔሪያሊስቶች ያደረጉት ርኩስ ጥረት ለተወሰነ ጊዜ የፈለጉትን ፍሬ አስገኝቶላቸው ነበር ።

ነገር ግን ንጋትና ውሃ እያደር ይጠራል እንደተባለው የአፍሪካ ተራማጆችና ጭቁን ሕዝቦች ፣ ሶሻሊስት አገሮችና የመላ ዓለም ጭቁን ሕዝቦች ይዋል ይደር እንጂ የዚህን ቃጠሎ ይዘትና ምንነት በትክክል መረዳታቸው የማይቀር ነገር ነበር ። እነዚህ ኃይሎች የኢትዮጵያን አብዮት ጠጋ ብለው ተመልክተው በዛሬው ወቅት መላ የዓለም ሕዝቦች ለሰላም በዲሞክራሲና ለሶሻሊዝም የሚደረገው ታሪካዊ ትጋድሎ የማይነጠል አካል እንደሆነ አመኑለት ። አቀፉት ። ደገፉት ። ከጐኑም ተሰለፉ ። በዚያው ልክ ደግሞ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመራራና የተወሳሰበ ትግሉ ተምሮ የተፋውንና ኢምፔሪያሊስቶች «ማርክሲስት» እያሉ የሚያሞካሹትን ኢ.ህ.አፓን የዓለም ተራማጆች ከዳር እስከዳር አወገዙት ። ስለጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት «ፋሽስትነት» ስለ ኢ.ህ.አ.ፓ. «ማርክሲስትነት» ኢምፔሪያሊስቶችና የውስጥ አድኃሪዎች የነዙት ፕሮፓጋንዳ በኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች አብዮት መግፋት የተነሣ ጨርሶ ተጋልጦ የማይሠራ ሆነ ።



የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት አብዮታዊነት ከተረጋገጠ አይቀር ፣ የዓለም ተራማጆች የአብዮታችንን ትክክለኛ ገጥታ ተገንዝበው ከጐኑ ከቆሙ አይቀር ፋሽስት እያሉ መጮሁ አላዋጣም ። ይልቁንስ «ኮሙኒስት» እያሉ «ማጥላላትና » የዓለም አድኃሪ ኃይሎች በሙሉ ኃይላቸውን አስተባብረው እንዲረባረቡበት መቀስቀሱ የሚያዋጣ ሆኖ አገኙት ። ጥር ፳፯ ቀን ተሞክሮ ከከሸፈው ሴራ በኋላ ኢምፔሪያሊስቶች በግልጽ የሚያስተጋቡት ፕሮፓጋንዳ ይዘት ይኸ ነው ። የአብዮቱን ምንነት እምነው ተቀብለዋል ። ከዳር እስካዳር የተለቀቁበት ፕሮፓጋንዳ ይዘት «ደርጉ የማያወላውል የማርክሲስት ሌኒንስት ፈር እየያዘ ሔደ» የሚል ነው ። ይኸ ደግሞ ላለው ሐቅ ተቆርቁረው ሳይሆን የዓለምን አድኃሪ ኃይሎችና ፀረ—ኮሙኒስቶች በሙሉ በተሻለ ይቀሰቅስልናል ብለው ስላመኑበት ነው ።

በኢ. ሕ. አ. ፓም በኩል አዲስ የተጀመረው ፕሮፓጋንዳ ይዘት ይህንኑ የታክቲክ ለውጥ የሚያንጸባርቅ ነው ። በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ መሐል ስርገው ያገቡት ቡችላቸው መሆኑን እያወቁ ፣ እቋሙ አቋማቸው መሆኑን እየተረዱ ፣ ቀደም ሲል ኢምፔሪያሊስቶች የሚነዙት ፕሮፓጋንዳ ኢ. ሕ. አ. ፓን «ማርክሲስት» አድርጎ የሚያቀርብ ፕሮፓጋንዳ ነበር እንዲውም ከዚህ አልፎ ተርፎ ባለፈው ጥቅምት ወር አንድ የኢምፔሪያሊስቶች ጋዜጣ «የኢትዮጵያ ችግሮች ማርክሲስቱ ኢ. ሕ. አ.ፓ ሥልጣን ካልያዘ አይፈቱም» ሲል ጽፎ ነበር ።

ነገር ግን ይህ ፕሮፓጋንዳ አልያዘም ። ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን መላ የዓለም ተራማጆች የዚህን አድኃሪ ድርጅት ማንነት ተረድተው ተፉት ። ኢምፔሪያሊስቶችም ይህ ቡድናቸው በሕዝቡ ከተተፋ አይቀር የዓለም አድኃሪዎች በይበልጥ እንዲያቅፉት ማድረግ ያስፈልጋል በሚለው ታክቲክ ቀረጡ ። የምን ማርክሲስት ? የምን አብዮታዊ ? ኢ. ሕ. አ. ፓ የተባለው ድርጅት የሀብታም ነጋዴዎችን የልጆቻቸው ጥርቃም መሆኑን እምነው የአድኃሪዎች ድጋፍ እንዳይለየው ይማጠኑበት ጀመር ።

ለለየለት ትግልና ፍልሚያ መሸጋሸግ ማለት ይኸው ነው ። ዛሬ በአብዮቱ ሠፈር ሆኖ ፋሽስት የሚባል ፣ በፀረ—አብዮቱ ሠፈር ቀሞ ማርክሲስት የሚባል ኃይል ሊኖር አይችልም ። ኢምፔሪያሊስቶች ይህንን ሐቅ ተገንዝበውታል ። የኢትዮጵያን አብዮት ለመቀልበስ በጠቅላላው ፀረ—አብዮት ኃይሎችንና በአገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ ማስተባበር እንዳለባቸው አውቀውታል። ችግሩ የሳውዲ ዓረብያን ነገሥታት ፣ ፀረ—ኮሚኒስቱን ኒሜሪ ፣ የኢትዮጵያን መሣፍንት በአፍ ደረጃ እንኳን ቢሆን «ማርክሲስት» ከሚባለው የግልገል መሣፍንት ቡድን ጋር ማስተባበሩ ላይ ነበር ። ማርክሲስት ያልነው ቀልድ ነበር ፣ የሀብታም ነጋዴዎችና የግልገሎቻቸው ቡድን ነው ብለው በይፋ መናገራቸው የፀረ አብዮቱን ሠፈር ለማስተባበር የሚደረገው ጥረት አንድ አካል ነው ።

ነገር ግን ይኸም ታክቲክ አይሠራም ። ይዘቱና ማንነቱ በይፋ የተረጋገጠለትም የኢትዮጵያ አብዮት በሚሊዮን የሚቆጠረው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከዳር ነቅቶ ተደራጅቶ እየታጠቀ የቆመለት አብዮት ነው ። በዓለም አቀፍ ደረጃም የአፍሪካ ተራማጆችና ጭቁኖች ፣ የሶሻሊስት አገሮችና የዓለም ተራማጆች በሙሉ የሚንከባከቡት አብዮት ሆኗል ። ኢምፔሪያሊስቶች የኢ. ሕ. አ. ፓን ማንነት በይፋ እምነው መውጣታቸው የአድኃሪዎችን ሠፈር ማጠናከር ያሉት ነው ። ነገር ግን በዚህ እምነት የአብዮቱ ሠፈር ይበልጥ ጥራት ስለሚያገኝ የማያቋርጥ ግስጋሴው ይፋጠናል ። የዚያኑ ያህል ደግሞ የአድኃሪዎች በማያዳግም ሁኔታ መደምሰስ የኢትዮጵያችን ሙሉ በሙሉ ነፃ መሆን ይቃረባል ።